# የኤች አይ ቪ ከእናት ወደ ልጅ መተላለፍ

«ኤች አይ ቪ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ የምንከተላቸው ዘዴዎች የጤና ስርዓትን ያጐለብታሉ፣ የኤድስን ተፅዕኖ ይቀንሳሉ እንዲሁም ህብረተሰቡ ኤች አይ ቪ ኤድስን ለመግታት እንዲነሳሳ ይረዳሉ» ዩኒሴፍ

የኤድስን ችግር በተለያየ መልኩ መመልከት ይቻላል:: በአለም ዙሪያ ያለውን የሴቶች ሁኔታ ስንመለከት በተለይ በአፍሪካ ለአስር በቫይረሱ ለተጠቁ ወንዶች አስራ አራት በበሽታው የተያዙ ሴቶች አሏቸው:: ተጽዕኖውን በአለም ዙሪያ ባሉ እንደ LGBT ማህበረሰብ ወይም የእየአካባቢው ተወላጅ የሆኑ ህዝቦችን በመውሰድ ማየት ይቻላል:: የቫይረሱ ከእናት ወደ ልጅ መተላለፍ ችግርም እንዲሁ::

ከእናት ወደ ልጅ መተላለፍ ትልቅ የኤች አይ ቪ ኤድስ መያዣ መንገድ ነው:: ይህ ሁኔታ በእርግዝና ወቅት በእትብት በኩል አልፎ ሊከሰት ይችላል:: ነገር ግን ብዙውን ጊዜ የሚተላለፈው በወሊድ ወቅት ወይንም እናትዮዋ ጡት በምታጠባበት ጊዜ ነው:: የኤች አይ ቪን ከእናት ወደ ልጅ የመተላለፍ እድል ለመቀነስ የሚያስችሉ በርካታ መንገዶች አሉ:: ለምሳሌ በቂ የባለሙያ ክትትል ያለበት ወሊድ በእናትዮዋና በሕፃኑ መካከል የደም ንክኪ እንዳይኖር ያግዛል:: ለዚህም እንዲረዳ የማዋለዱ ሂደት በብልት በኩል ከሚሆን ይልቅ በሌሎች ዘዴዎች ሊከወን ይችላል:: ይህ አይነቱ ዘዴ ጠንካራ የህክምና አቅምን ይጠይቃል፤ በተለይ 95 በመቶ የሚሆኑት ኤች አይ ቪ ፖዘቲቭ ነፍሰጡር ሴቶች ለሚገኙባት አፍሪካ::

የጡት ማጥቢያ ጊዜን ማሳጠር ወይንም ጭራሽኑ አለማጥባት የኤች አይ ቪ ከእናት ወደ ልጅ የመተላለፍ ሁኔታን በእጅጉ ይቀንሳል:: ነገር ግን ይህ ዘዴ ሌሎች በርካታ ጥያቄዎችን ያስነሳል:: አንደኛ:- ለአፍሪካ ሴቶች ልጆቻቸውን እስከ ሁለት አመት ድረስ ማጥባት በጣም የተለመደ ነው:: ምክንያቱም ወሊድን ለመቆጣጠር ስለሚያስችል:: የጡት ማጥቢያ ጊዜው ወደ ስድስት ወር ዝቅ ቢደረግ የቫይረሱን የመተላለፍ ሁኔታ በሁለት ሶስተኛ ይቀንሳል:: ነገር ግን የልማዶች ለውጥ የባሕል እሴቶችን መለወጥ ማለት መሆኑ መረሳት የለበትም:: ለአፍሪካውያን ሴቶች ጡት ማጥባት ለልጆቻቸው ጤናማው ዘዴ ነው፤ በቆሻሻ ውሃ ከሚበጠበጠው የዱቄት ወተት ጋር ሲነፃፀር ሕፃኑን ከባክቴሪያ ስለሚከላከል:: በታዳጊ ሀገሮች የሚገኙ የዱቄት ወተት ፋብሪዎች የሚከተሉት ስልት በግልጽ ይታወቃል:: ጥቂት ፋብሪካዎች የዱቄት ወተት ጣሳዎችን በ«አናሳ ቋንቋዎች» ወይም በስዕላዊ መግለጫዎች ባለማተማቸው በአለም አቀፍ የጤና ድርጅት ተደጋጋሚ ወቀሳ ቀርቦባቸዋል::

የዱቄት ወተት ዋጋ ከፍተኛ ስለሆነ ወላጆች በዱቄቱ ላይ ብዙ ውሀ ስለሚጨምሩበት ካለማወቅ ህፃናት ይራባሉ፡፡ ብዙውን ጊዜ ተቅማጥ እና የአልሚ ምግቦች እጥረት በጣም ቀጭን ወተት ከመጠጣትና በተበከለ ውሃ የተበጠበጠ ወተት ከመመገብ ጋር ይያያዛል፡፡ ቀደም ሲል ልጅን ጡት ማጥባት ጥሩ ነው ተብለው የነበሩ ደሀ ሴቶች አሁን ደግሞ የጡታቸው ወተት ልጆቻቸውን በኤች አይ ቪ እንዲያዙ ያደርጋል እየተባሉ ነው፡፡ ይሁንና ጡት ያልጠቡ አዲስ የተወለዱ ህፃናት በመጀመሪያዎቹ ሁለት ወሮች የመሞት እድላቸው ስድስት እጥፍ ነው፡፡ በጡት ማጥባት የሚመጣውን የቫይረስ መተላለፍ ለመግታት ህፃኑ በቀጥታ ጡቱን እንዳይጠባው ማድረግ ይቻላል፡፡ ነገር ግን በቀላሉ የማይገኙ የህክምና መሳሪያዎችን ይጠይቃል፡፡ እንደ ብራዚል ባሉ ሀገሮች የጡት ወተት ባንክ፣ በእርጥበት ቦታ ማድረግ እና ሕፃኑ ከመመገቡ በፊት ወተቱን «በጨረር» ማሞቅ የመሳሰሉ የፈጠራ መፍትሔዎች ተገኝተዋል፡፡ አሁንም ቢሆን ግን ለእናቶች ትምህርትና ድጋፍ በስፋት መስጠት ያስፈልጋል፡፡

ነፍሰጡር ኤች አይ ቪ ፖዘቲቭ ሴቶችን በተመለከተ ተቀባይነት ያለው ሕክምና ከወሊድ በፊትና በወሊድ ወቅት «አንቲሬትሮቫይራል» የተባሉ መድሀኒትቶች መውሰድ ነው፡፡ የእነዚህ መድሀኒቶች ውጤታማነት ባይካድም በአጠቃቀም ዙሪያ ከፍተኛ አለመግባባቶች አሉ፡፡ በርካታ አፍሪካውያን መድሀኒቶች ለኤድስ ህክምና ያግዛሉ ብለው አያምኑም፤ የመድሀኒቶች አጠቃቀምን በተመለከተ መረጃ አያገኙም፤ ለመድሀኒቶች መውሰጃ ንፁህ ውሃ ለማግኘትም ይቸገራሉ፡፡ በተጨማሪም የቫይረሱን ከእናት ወደ ልጅ የመተላለፍ እድል ለመቀነስ የሚሰጡት መድሀኒቶችም በህዝብ ጤና ላይ ችግሮች የሚፈጥሩበት ሁኔታ አለ፡፡ ለምሳሌ AZT የተባለው መድሀኒት በጤና ላይ ጉዲ ጉኖች አሉት የሚሉ ጥርጣሬዎችን አስነስቷል፡፡ ሌላው በአፍሪካ ኤድስን ለመዋጋት እንቅፋት የሆነው ጉዳይ ብዙውን ጊዜ ከቻይና የመድሀኒት ፋብሪካዎች የሚመረቱ ውጤታማ ያልሆኑ /ፈዋሽነት የሌላቸው/ መድሀኒቶች ወደ አህጉሪቱ መግባት ነው፡፡ እነዚህን መድሀኒቶች የወሰዱ እናቶች ለሞት ይዳረጋሉ፡፡ ይህም በመድሀኒት ህክምና ጠቀሜታዎች ላይ ከፍተኛ ጥርጣሬ ያሳድራል፡፡

የመድሀኒቶች ዋጋም ሌላው ጉዳይ ነው፡፡ ለምሳሌ «ኔቪራፒኔ» የተባለው «አንቲሬትሮቫይራል» 8 የአሜሪካ ዶላር ያወጣል፡፡ ይህም ማለት በተወሰኑ የአፍሪካ አካባቢዎች የአንድ ሰው የወር ደመወዝ ያክል ነው፡፡ የ«አንቲሬትሮቫይራሎች» መወደድ ከአመኔታ ማጣትና ከመረጃ ክፍተት ጋር ተዳምሮ በሺዎች የሚቆጠሩ የአፍሪካ ሴቶችን የጤና ህክምና እንዳያገኙ አድርጓቸዋል፡፡ በተጨማሪም ኤች አይ ቪ «ኔቪራፒኔ»ን ሊቋቋመው ይችላል የሚል ማስረጃ አለ፡፡

ሴቶች ኤች አይ ቪ ፖዘቲቭ ከሆኑ የቫይረሱን ከእናት ወደ ልጅ መተላለፍ ለመቀነስ የሚያስችሉ ዘዴዎች ከላይ የተጠቀሱት ናቸው:: ነገር ግን ይህ ጥንዶች በቫይረሱ እንዳይያዙ የመከላከል እና ኤች አይ ቪ ፖዘቲቭ የሆኑ ሴቶችን ካልተፈለገ እርግዝና የመጠበቅ አካል ነው:: የታቀደ እርግዝና ከሆነ የቫይረሱን ከእናት ወደ ልጅ የመተላለፍ ችግር በአጥጋቢ ሁኔታ ለመቀነስ ይቻላል::

በአለም ዙሪያ አንድ በመቶ የሚሆኑ ነፍሰጡር ሴቶች ኤች አይ ቪ ፖዘቲብ እንደሆኑ ይገመታል:: ከነዚህ መካከል ሁሉም ማለት ይቻላል የህክምና አቅርቦት እጥረት ባለባቸው ታዳጊ ሀገሮች የሚኖሩ ናቸው:: በአሁኑ ወቅት በየአመቱ 700 000 ህፃናት ከእናታቸው ማህፀን ውስጥ እያሉ፣ በወሊድ ወቀት ወይም በእናት ጡት ወተት አማካኝነት በኤች አይ ቪ ይያዛሉ:: በአለም አቀፍ ደረጃ አምስት ሚሊዮን ኤች አይ ቪ ፖዘቲቭ ልጆች አሉ፤ ከነዚህም ውስጥ 90 በመቶ የሚሆኑት በታዳጊ ሀገሮች የሚኖር ናቸው:: ይህም ወደፊት የሚኖረውን ተጽዕኖ በቀላሉ ለመገመት ያስችላል:: ጤናማ ካልሆነች እናት የሚወለዱ ልጆች በለጋ እድሜያቸው አሳዳጊ የሌላቸው ሊሆኑ ይችላሉ፣ እናም በድህነት ያድጋሉ፣ የትምህርት እድልም ይነፈጋሉ:: በኤድስ ምክንያት ወላጆቻቸውን ላጡ ህፃናት ወደ ጐዳና መውጣት ወይም በስርቆትና በሴተኛ አዳሪነት መሰማራት የተለመደ የሕይወት መስመር ነው:: በደቡብ አፍሪካ ብቻ ከአንድ ሚሊዮን በላይ ወላጆቻቸውን በኤድስ ያጡ ህፃናት ይገኛሉ:: ልጆቹ እራሳቸው ኤች አይ ቪ ፖዘቲቭ ከሆኑ ደግሞ በህይወት የመኖር ተስፋቸው የመነመነ ይሆናል:: እንደ ኢኮኖሚና ህክምና ቀውስ ሁሉ የከፋ ችግር ነው::

ከ25 አመት በታች ካሉ አምስት ሴቶች አንዷ ኤች አይ ቪ ፖዘቲቭ በሆነባት አፍሪካ ብዙሀኑ የችግሩ ተጠቂ የሚሆንበት ደረጃ ላይ ተደርሷል:: ጡት በማጥባት ዙሪያ የተለያዩ አመለካከቶች መኖራቸው እንዲሁም የመረጃ እጥረት ችግሩን እያባባሱት ስለሆነ መፍትሄ ለመሻት ያስቸግራል:: ዝምታውን ለመስበርና በሽታውን በተመለከተ ብዥታዎችን ለማጥራት ሲባል ለሁሉም ወላድ ሴቶች ሚስጥራዊነቱ የተጠበቀ የኤች አይ ቪ ምርመራና ምክር ለመስጠት ታቅዷል:: እንደ ቦትስዋና እና ሌሶቶ ባሉ አንዳንድ የአፍሪካ ሀገሮች በእርግዝና ወቅት ምርመራ ማድረግ ግዴታ እየሆነ ነው:: ይህ ዘዴ በአሜሪካ የበሽታዎች መቆጣጠሪያ ማዕከል ተቀባይነት አለው:: ሁሉም ስልቶች ለነፍሰጡር ሴቶችና ለልጆች ጤንነት ስለሚያግዙ ስለ ምርመራና እንክብካቤ እናቶችን ማስተማርና ማብቃት ጠቃሚ ነው::